information

refugee action

working with refugees to build new lives

# Section 4 NASS* ድጋፍ

## የSection 4* ድጋፍ ለማን ነው የሚሰጠው?

ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ነገሮችን በሙሉ የሚያሟሉ ከሆነ የSection 4* ድጋፍ የማግኘት መብት አልዎት፥

- ጥገኛ ፈላጊ ከነበሩ፡ እና
- ለጥገኝነት ያቀረቡትን ማመልከቻ ተቀባይነት ካላገኘ፡ እንዲሁም
- ሌላ ምንም የድጋፍ ምንጭ ከሌልዎት
- የይግባኝ ማመልካቻ ካስገቡ፡ ድጋፍ የማግኘት መብት አልዎት። እባክዎትን ይጠይቁን።

ቀጥሎ ከተዘረዘሩት ደግሞ አንዱን የሚያሟሉ ከሆነ፥

- የጉዞ ይለፍ ወረቀት ለማግኘት አመልክተው ከሆነና (ይህም ከኤምባሲዎ / ከየኢሚግሬሽን አገልግሎት) ወይም ደግሞ በፈቃደኝነት ለመመለስ አመልክተው፡ ከመመለስዎ በፊት፡ ስለ መንገድዎ የመጨረሻ ዝርዝር ውሳኔ ለማግኘት እየጠበቁ ከሆነ፡
- በሕክምና ምክንያት ከእንግሊዝ አገር ለመውጣት የማይችሉ ከሆነ፡
- Home Office* ወደ አገርዎ የሚመለሱበት መንገድ አደገኛ ነው ብሎ ካሰበ
- የጥገኝነት ጥያቄዎ በተመለከተ የJudicial Review* ለማግኘት ፍቃድ የተሰጡ ከሆነ
- የውስጥ ጉዳይ ሚኒስተሩ፡ እርስዎ ያለድጋፍ፡ ቢኖሩ ያልዎትን የሰብአዊ መብቶችን እንደመጣስ ነው ብሎ ካመነ - ለምሳሌ፡ ጠበቃዎ ጉዳይዎን ለ further representations* ካቆየ፡ ወይም ደግሞ እስር ቤት ውስጥ ካሉ፡

## የ Section 4* ድጋፍ ምንድን ነው?

- በ NASS* የሚሰጥ የመኖርያ ቤቶች፡ ከዚህም ጋር አብዛኛው ግዜ ለምግብ እና ከሌሎች ትናንሽ ነገሮች ተብሎ የ £35 ቫውቸር ይሰጣል
- ሌላ የጥሬ ገንዘብ ድጋፍ የሌለበት
- የሚሰጠው የመኖርያ ቤት ደግሞ አብዛኛው ጊዜ እርስዎ ባሉበት አከባቢ ላይ ይሆናል፡ ነገር ግን ከሚኖሩበት መኖርያ ቤት ወጥተው ወደዛ ሊገቡ ይችላሉ
- እነዚህ እላይ የተጠቀሱትን መመዘኛዎች የሚያሟሉ መሆንዎን ለማረጋገጥ NASS* እንደገና ይመረምራል፤ ይህንን የማይመለከትዎ ከሆነ ደግሞ እርዳታውን ያቋርጣል (ለምሳሌ፡ በፈቃደኝነት ለመመለስ ያስገቡትን ማመልከቻ ከቀየሩት፡ ድጋፉ ሊሰረዝ ይችላል)።

## እንዴት ማመልከት እችላለሁኝ?

- እባክዎ፡ በአቅራቢያዎ ወደ የሚገኘው የምክር ኤጀንሲ ይሂዱ - ወደ NASS* ለማመልከት ፎርሙን በሞሙላት ረገድ ያግዝዎቷል
- NASS* የSection 4* የድጋፍ አሰራር ሁኔታ ገብቶኛል የሚለውን ፎርም ላይ እንዲፈርሙ ይጠይቆቷል - ይህንን በኃላ ልንገልጸው ነው።
- አንዴ ካመለከቱ በኃላ፡ NASS* የSection 4* ድጋፍ ይሰጥዎቷል ወይም አይሰጥዎትም ለማወቅ ትንሽ ጊዜ ይወስዳል።
- NASS* የSection 4* ድጋፍ ከሰጥዎት በኃላ፡ ወደ መኖርያ ቤቱ ለመግባት ሌላ የአንድ ሳምንት ጊዜ ሊወስድ ይችላል።

*እነዚህ ቃላቶች የአንዳንድ ድርጅቶች የእንግሊዘኛ ስሞች፡ ወይም ደግሞ ሌሎች መተርጎም የሌሌባቸው ቃላቶች ናቸው። ምን ማለት መሆናቸውን እንዲገልጽልዎት እባክዎን ምክር የሚሰጠውን ሰራተኛ ይጠይቁ።

**እባክዎን ማንኛውም ዓይነት አስተያየት ጥያቄ ካልዎት፡ ይጠይቁ።**